PHASE 2

# ዉስጥ ግብይት መሳሪያዉ




City of Seattle

#SupportSeattleSmallBiz
#WeGotThisSeattle

# ማጠቃለያ

## ዙር 2 ምንድነው?

ዙር 2 አንዳንድ ንግድ ድርጅቶችንና ተግባራትን በጥብቅ የማህበረሰብ ጤናና ደህንነት መመሪያ መሠረት እንድቀጥሉ ይፈቅዳል። የተለየ ተጨማሪ መመሪያ የሚፈልጉ የንግድ ድርጅት ባለቤቶች በዋሽንግተን ግዛት የኮሮናቫይረስ መልስ መስጫ ገጽ (በእንግልዝኛ ብቻ) ድጋፍ መጠየቅ ይችላሉ፤ የዋሽንግተን ስቴት ሥራና ኢንደስትሪ ዘርፍ በ1-800-547-8367 ይደዉሉ የትርጉም አገልግሎት አለ ወይንም የከተማዉ የኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሠራተኛ በ206-684-8090 ያግኙ የትርጉም አገልግሎት አለ።

የግል አገልግሎቶች ማለት የዉበት ባለሙያዎች፣ ጸጉር ሠሪዎች፣ ጸጉር አስተካካዮች፣ የቆዳ ዉበት በለሙያዎች፣  ማስተር የቆደ ዉበት በለሙያዎች፣ የጥፍር ዉበት በለሙያዎች፣ የጥፍር ሳሎን ሠራተኞች፣ በኤሌክትሪክ ጸጉር ነቃይ ባለሙያዎች፣ ቋሚ የሜካፕ አርትስቶች፣ የንቅሳት አርትስቶች፣የዉበት ባለሙያ ትምህርት ቤቶችና የቆዳ ዉበት ባለሙያ ትምህርት ቤቶች።

## ዙር 2 መቼ ነው የሚጀምረዉ?

ኪንግ ካዉንቲ በሰኔ (ጁን) 19ኛ ቀን ወደ ዙር 2 ገብቷል። የጤና ቢሮ እነዚህን ልዩ መብቶች በማንኛዉም ሰዓት ማንሳት ይችላል። ላምሳሌ በ COVID-19 የተያዙ ሰዎች ቁጥር ብጨምር ወደ ዙር 1.5 ወይንም ዙር 1 ልንመለስ እንችላለን።

## ለድርጅቴ ዙር 2 ማለት ምን ማለት ነው?

በዙር 2 መመሪያ የንግድ ሥራዎትን ለማከናወን የተወሰኑ የጤናና ደህንነት መስፈርቶችን መከተል አለብዎት፤ እነዚህም በዚህ ሳይገደቡ የምጨምሩት፡

- ህንጻዉ መያዝ ከሚችለዉ 30 ፐርሰንት ባልበለጠ መሥራት በኢሳት ደንብ እንደተወሰነዉ ና
- ያለንኪክ የክፍያ አማራጮችን፣ ሲቻል ዕቃዎችን ማንሳት እና/ወይንም  ማድረስን ያዘጋጁ።

## ተጨማሪ መረጃ ከየት ማግኘት እችላለሁ?

ከተማዉ ከስቴት የሚመጠዉን መረጃ በተቻለ ፍጥነት ማስተላለፉን ይቀጥላል። ማንኛዉም ከተማዉ ያዘጋጃቸዉ ሰነዶች ተደራሽና በቋንቋ ይቀርባሉ። እስከዚያዉ ለተጨማሪ መልሶ የመክፈት መመሪያ የዋሽንግተን ስቴት ሥራና ኢንዱስትሪ ዘርፍ ድህረ ገጽ (በእንግልዝኛ ብቻ) መጎብኘት አለብዎት። የገዢዉ ዙር 2 የሱቅ ዉስጥ ግብይት መመሪያንም (በእንግልዝኛ ብቻ) ከዚህ ከዚህ ማግኘት ይችላሉ፤ በተጨማሪም የገዢዉ የዋሽንግተን በደህንነት የመጀመር ዕቅድ (በእንግልዝኛ ብቻ) ከዚህ ያገኛሉ።

የሲያትል ከተማ ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ (ኢልቢ) ለጥቃቅን ንግድ ድርጅቶች፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ፣ ና በCOVID-19 ተጽዕኖ ለደረሰባቸዉ ሠራተኞች አጠቃላይ የድጋፍ ምንጭ ገጽ አለዉ።

በተጨማሪም የሲያትል ስራ ድረጃዎች ቢሮ ስለ በሲያትል የህመምና የደህንነት ግዜ ክፍያ ( Seattle's Paid Sick and Safe Time (PSST)) ህግ ስር ያሉትን ኃላፊነቶችዎ ተጨማሪ መረጃ አለዉ፤ በፌደራል ቤተሰሰቦች ቅድሚያ ኮሮናቫይረስ ምላሽ ደንብ ( federal Families First Coronavirus Response Act (FFCRA)) ስር ያለ ከ COVID-19 የተገነኘ የዕረፍት ክፍያም ጭምር። ሁለቱም   FFCRA ዕረፍትና  PSST ሠራተኞችና ልጆች ሲታመሙና በማህበረሰብ ጤና ድንገተኛ ግዜ ከሥራ ባልደረቦች፣ ትምህርት ቤት፣ ና ደንበኞች ርቀዉ ቤት መቀመጥ እንዲችሉ በማረጋገጥ የማህበረሰብ ጤናን ይጠብቃል። ስለ  PSST ተጨማሪ መረጃ እዚህ የሲያትል ስራ ደረጃዎች ቢሮ PSST  COVID-19 ጥያቄና መልስ መጎብኘት ይችላሉ (በበርካታ ቋንቋዎች ከዚህ አለ)። ስለ  FFCRA COVID-19 ዕረፍት ተጨማሪ መረጃ እዚህ ይገኛል (በእንግልዝኛ ብቻ)።

# ወደ መሰሪያዉ ይሂዱ!

ይህ በሲያትል ከተማ የተመረተ የድጋሚ መክፈቻ መሣሪያ ነዉ፤ በግዛቱ ጤና ቢሮና በሲያትልና ኪንግ ካዉንቲ ማህበረሰብ ጤና በወጡ መመሪያዎች የተመሰረተ የድርጅት ባላቤቶችን በዙር 2 በተሳካ ሁኔታ እንዲከፍቱ ለመርዳት ተደራሽ ከፍተኛ ደረጃ መረጃ ለማቅረብ የታሰበ ነዉ። ሁሉም መመሪያዎች በየትኛዉም ግዜ ልቀየሩ ይችላሉ።

**በዙር 2 የሱቅ ዉስጥ ግብይት ደህንነቱ በተጠበቀ የመጀመር ዕቅድ ወቅት ንግድ ድርጅቶች በ30 ፐርሰንት የህንጻ አቅማቸዉ እንድሰሩ ተፈቅዶላቸዋል፤ በተጨማሪም ለማንሳት/ማድረስ ና ያለንክኪ ክፍያ አማራጮች ቅድሚያ መስጠት አለባቸዉ።**

3

# ዙር 2 የሱቅ ዉስጥ ግብይት ዝርዝር ተግባራት

## የሠራተኞች ጤናና ደህንነት

ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ ከባቢያዉ ሁኔታ መቅረቡን ማረጋጋጥና ሠራተኞችን ስለ አመላካቾች፣ የህመም ምልክቶች ና ከCOVID-19 ህመም ጋር የተያያዙ የስጋት ምክንያቶች፣ እንዴት የኮሮናቫይረስ ስርጭትን ሥራ ቦታ መከላከል እንደሚቻል ማህበራዊ ርቀትን ሥራ ቦታ ላይ ለማቋቋም የተወሰዱ እርምጃዎችን፣ በየግዜዉ እጅ መታጠብን ና ሌሎች ጥንቃቄዎችን ጨምሮ ማስተማር። የማህበረሰብ መመሪያዎችን ከ30 ቋንቋዎች በላይ ለማግኘት www.kingcounty.gov/covid ይጎብኙ።




- ☐ ሠራተኞች የ6 ጫማ አካላዊ ርቀት እንዲጠብቁ ያረጋግጡ። ያ ከልተቻለ የስራ ሰዓቶችን ያሰባጥሩ ወይንም በሠራተኞች መካከል ከለላ ያስቀምጡ።



- ☐ ለሠራተኞች ነጻ የፊት መሸፈኛና ተጠቅመዉ የሚጥሉት ጓንት ያቅርቡ። ለራስዎና ሠራተኞችዎ የፊት መሸፈኛዎችን ለማግኘት seattle.gov/mayor/covid-19/seattle-protects ይጎብኙ።



- ☐ በየግዜዉ እጅ መታጠብን



- ☐ ለያንዳንዱ ሽፍት ብቸኛዉ ሚናዉ የሠራተኛ ጤናና ደህንነት እና ባግባቡ የጽዳት፣ የንጽህና ና የመለየት አሰራሮች መከተላቸዉ ማረጋጋጥ የሆነ የCOVID-19 ተቆጣጣሪ ይመድቡ።




- ☐ እያንዳንዱ ሠራተኛ ለሥራ እንደመጣ ወዲያዉ ሙቀት ይለኩና ሠራተኞችን የCOVID-19 ምልክቶች እንዳለባቸዉ ይለዩ። ሠራተኛ ምልክቶችን ካሳየ ወዲያዉ ወደ ቤት ይላኳቸዉና ያ ሠራተኛ የነካቸዉን ሥፍራዎች/ገጾች በደንብ ያጽዱ።




- ☐ የ COVID-19 ደህንነት መረጃና መስፈርቶች በምታይ ሁኔታ ይለጠፍ።



- ☐ ወደ ድርጅቱ ዋና መግቢያ በፊትለፊት በር መሆን አለበት፤ ወደ ኋላ በር ወይንም ሌሎች የመግቢያ በሮችን ሰዉ እንዳይደርስ ይገድቡ። መግባት የሚቻልበት በር የፊትለፊት በር ካልሆነ መግባት የሚቻልበትን መግቢያ ይፍቀዱ።

## Customer Health and Safety

ተቋሞ ዉስጥ በተለያዩ ቦታዎች በብዙ ቋንቋዎች ወቅታዊ የሆነ የማህበረሰብ ጤና መመሪያ እንዲታይ ያስቀምጡ። በነጻ ከ www.kingcounty.gov/covid ሊወርዱ የሚችሉ ከ30 በላይ በሚሆኑ ቋንቋዎች የሲያትልና ኪንግ ካዉንቲ ማህበረሰብ ጤና ፖስተሮች ይገኛሉ።




- ☐ መጠበቅ ሊኖር የሚችል ከሆነ በህንጻዉ ዉስጥ ና ዉጪ የ6 ጫማ አመልካከቾችን ያስቀምጡ፤ የደንበኞችን ፍሰት የሚቆጣጠር ሠራተኛ ይመድቡ።



- ☐ በሱቁ ዉስጥ ሁሉ ቦታ የማህበራዊ ርቀት ና የሰዉ ብዛት መስፈርቶች ምልክቶች ያስቀምጡ።



- ☐ በብዛት ጥቅም ላይ የሚዉሉ ሥፍራዎችን፣ መጸዳጃ ክፍሎች፣ ና ማንኛዉም ሠራተኞች የሚጠቀሟቸዉን መሣሪያዎችን በተደጋጋሚ ያጽዱና ሳኒታይዝ ያርጉ (ጀርም ያስወግዱ)።



- ☐ ከተቻለ በከፍተኛ ተጋላጭ ለሆን ግለሰቦች የተመደበ ሰዓት ይኑሮት።



- ☐ ከያንዳንዱ መጠቀም በኋላ የመልበሻ ክፍሎች መጽዳት አለባቸዉ።




- ☐ ወደ መሸጫ ወለል ከመመለሳቸዉ በፊት የመልበሻ ክፍሎች ዉስጥ የተተዉ ያልተገዙ ዕቃዎች ከ24 ሰዓታት ላላነሰ ግዜ መጠራቀም አለባቸዉ ።



- ☐ ግንኙነት ያለዎትን ሰዎች ክትትልን ለማቀናጀት እንዲረዱ በጎ ፈቃደኛ የሆኑ ደንበኞች ዝርዝር ለማስቀመጥ ያስቡ። ዝርዝሩ ማካተት ያለበት ስም፣ ስልክ ቁጥር፣ ና ድርጅቱን የጎበኙበት ቀን።

## ስለ ትብብርዎ እናመሰግናለን!

# ከቤት ውጭ የፍቃድ አማራጮች በጨረፍታ

ኪንግ ካውንቲ የገዥውን ደህንነቱ የተጠበቀ  ጅማሬ እቅድ ምዕራፍ ሁለት ላይ ስለገባ ፣ ብዙ የንግድ ባለቤቶች ከቤት ውጭ ሥራቸውን እንደገና ለመክፈት ወይም ለማስፋት እንደሚጓጉ እናውቃለን ፣ ስለሆነም እርስዎን ለማስጀመር ይህንን የመረጃ ወረቀት ፈጥረናል!

## በመንገድ ላይ ወይም በእግረኛ መንገድ ላይ ከቤት ውጭ ንግድዎን ስለ መጨመር ወይም ማስፋት

በንግድ ቦታዎ ፊት ለፊት በሚገኝ እግረኛ መንገድ ላይ ወይም በጎዳና ላይ ቦታን በመጠቀም ጊዜያዊ ካፌን ወይም ተጨማሪ የችርቻሮ ቦታን ለመጨመር ፍላጎት ካለዎት ወይም አዲስ የሽያጭ አካባቢዎችን ለመሞከር የሚፈልጉ የምግብ እና የጭነት ጋሪ ባለቤት ከሆኑ ከሲያትል ትራንስፖርት ዲፓርትመንት (SDOT) የጎዳና አጠቃቀም ፈቃድ ያስፈልጎታል ፡፡

ለእግረኛ መንገድ ካፌዎች ፣ ለሽያጭ ዕቃ ማሳያዎች እና ለምግብ እና ለሌላ ሽያጭ አዲስ ተለዋዋጭ ጊዜያዊ የፍቃድ አማራጮችን ፈጥረናል ፡፡ እነዚህ ፈቃዶች እስከ ስድስት ወር ድረስ ጥሩ ናቸው።

- **ጊዜያዊ ከቤት ውጭ ካፌ ፈቃድ:** በእግረኛ መሄጃው ላይ ወይም በእግረኛ ማቆሚያ ቦታ ላይ መቀመጫዎችን መጠቀም የሚፈልግ ምግብ ቤት ባለቤት ከሆኑ ይህንን ፈቃድ ይጠይቁ። የአልኮል መጠጥ ለማቅረብ ተጨማሪ የ ዋሽንግተን ግዛት ፈሳሽ እና የካናቢስ ቦርድ  ፍቃድ ይጠየቃል ፡፡
- **ጊዜያዊ የግብይት ማሳያ ፈቃድ:** የንግድ ክወናዎችን ወደ የእግረኛ መንገዱ ላይ ወይም የተከለለ ማቆሚያ ቦታ ውስጥ ለማስፋፋት የሚፈልጉ የችርቻሮ ንግድ ባለቤት ከሆኑ ይህን ፈቃድ ይጠይቁ (ይህ የሽያጭ እንቅስቃሴን እንደሚያካትት ልብ ይበሉ)).
- **ጊዜያዊ የሽያጭ ፈቃዶች:** በሽያጭዎ አካባቢ እና ቆይታ ላይ የበለጠ ተለዋዋጭነት እንዲኖር የሚፈልጉ ሻጭ ከሆኑ ይህንን ፈቃድ ይጠይቁ። ይህ መንገድ እና የእግረኛ መሄጃ ቦታ የምግብ ጭነት መኪናዎች እና ጋሪዎችን ያጠቃልላል ፡፡

እባክዎን ያስታውሱ ምግብ ቤቶች እና የችርቻሮ ንግድ ሥራዎች የፍቃድ መስፈርቶችን ለማሟላት አስፈላጊ አጥርን ሁሉ ማቅረብ አለባቸው ፡፡ የፍቃድ ክፍያዎች  በግምት $ 320 ናቸው (የግምገማ እና የፍተሻ ክፍያዎችን ጨምሮ)። እኛ እነዚህን ዓይነት የፍቃድ ማመልከቻዎች እናፋጥናለን ቅድሚያም እንሰጣለን ፣ ሆኖም እንደ በፍቃዱ አተገባበር ጥራት ፣ የቦታው ውስብስብነት እና በጥያቄዎች ብዛት ላይ በመመርኮዝ ተጨማሪ የግምገማ ጊዜ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

ሁሉም ሥፍራዎች ለእነዚህ ፈቃዶች ብቁ ባይሆኑም ሌሎች ዕድሎችን ለመለየት ከእርስዎ ጋር በመሰራታችን ደስተኞች ነን!

## በግል ይዞታዎ ላይ ከቤት ውጭ ንግድዎን ስለ መጨመር ወይም ማስፋፋት

በንብረትዎ ውስጥ ለንግድ ሥራዎች ከቤት ውጭ ቦታ ለመመስረት ወይም  በይዞታዎ ላይ ከቤት ውጭ በሚገኝ ቦታ የንግድ ሥራዎችን ለመመስረት ወይም ለማስፋፋት ፍላጎት ካለዎት ከሲያትል የግንባታና ምርመራ ክፍል (SDCI) ከሚከተሉት ፈቃዶች ውስጥ አንዱ ሊያስፈልግዎት ይችላል ፡፡.

- **ቋሚ አጠቃቀም ፈቃድ:** ከቤት ውጭ ቦታው ከመኖሪያ አከባቢ ከ 50 ጫማ በላይ የሚገኝ ከሆነ እና በከተማው ውስጥ የመሬት አጠቃቀም ሕግ መሰረት ሌሎችንም መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ ይህንን ፈቃድ ይጠይቁ ይህ ፈቃድ አዲሱን ከቤት ውጭ ቦታዎን በቋሚነት እንዲጠቀሙ ይፈቅድልዎታል ፡፡
- **ጊዜያዊ አጠቃቀም ፈቃድ:** ከቤት ውጭ ቦታው ከመኖሪያ አካባቢው ከ 50 ጫማ በታች ከሆነ ወይም ከሌላ የመሬት አጠቃቀም ኮድ መስፈርቶች ተለዋዋጭ እንዲሆኑ ከፈለጉ ይህንን ፈቃድ  ይጠይቁ ፡፡ ይህ ፈቃድ የቤት ውስጥ ቦታዎን ለአራት ሳምንታት እንዲጠቀሙ ይፈቅድልዎታል ፣ ግን እንደገና ማመልከትዎን መቀጠል ይችላሉ ፡፡
- **ጊዜያዊ አጠቃቀም ፈቃድ:** ከቤት ውጭ ቦታው ከመኖሪያ አካባቢው ከ 50 ጫማ በታች ከሆነ ወይም ከሌላ የመሬት አጠቃቀም ኮድ መስፈርቶች ተለዋዋጭ እንዲሆኑ ከፈለጉ እና በየሳምንቱ አንድ ጊዜ ወይም  ሁለት ቀናት ብቻ ከቤት ውጭ መጠቀም የሚፈልጉ ከሆነ ይህንን ፈቃድ ይጠይቁ ፡፡ ይህ ፈቃድ ለአንድ ዓመት ያህል ጥሩ ነው ፡፡

የፍቃድ ክፍያዎች በግምት $ 350 ናቸው። እንደነዚህ ዓይነቶችን የፍቃድ ማመልከቻዎችን እያፋጠን እና ቅድሚያ እየሰጠን ነው : : የፍቃድ ማመልከቻው ጥራት ላይ በመመስረት ፈቃዶች ለማግኘት እስከ ሶስት ሳምንታት ሊወስድ ይችላል

## እገዛ ይፈልጋሉ ወይም ስለ አማራጮችዎ ጥያቄዎች አልዎት?

ስላሉት የተለያዩ ፈቃዶች ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም በማመልከቻው ሂደት ላይ እገዛ ከፈለጉ ፣ በ 206-684-8090 ይደውሉልን ወይም በነጻ እገዛ እና ቴክኒካዊ ድጋፍ በ oed@seattle.gov ይላኩልን ፡፡

በ ግል ንብረት ላይ ስላሉ  የቤት ውጭ ፈቃዶች ተጨማሪ መረጃ በ SDCI ድእረ ገፅ ላይ  www.seattle.gov/sdci/permits/how-do-you-get-a-permit.

በጎዳናዎች እና በእግረኛ መንገዶች ላይ ለቤት ውጭ ፈቃድ ፣ በ SDOT ድእረ ገፅ ላይ የበለጠ መረጃ ያገኛሉ www.seattle.gov/transportation/permits-and-services/permits/temporary-permits ላይ ማግኘት ይችላሉ

City of Seattle

# ሌሎች የድጋፍ ምንጮች

ስልሚከተሉት መረጃ ጥያቄዎች ካለዎት ለነዚህ ተቋማት ይደዉሉላቸዉ። ሲደዉሉ የቋንቋ ድጋፍ ከፈለጉ በእንግልዝኛ የሚመርጡትን ቋንቋ ይንገሩን። ወይ ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ሠራተኛ መልሶ ይደዉልሎታሎ ወይንም ሶስተኛ ወገን አስተርጓሚ በመነጋገሩ እንድረዳዎት በስልክ እንጠራለን።

እባክዎን ብዙ ሰዎች እንድንረዳቸዉ ይደዉሉልናል፤ ስለዚህ ረጅም ግዜ ሊጠብቁ እንደምችሉ ያስቡ። ከአስተርጓሚ ጋር ስናገናኞትም ሊጠብቁ ይችላሉ።

| አርእስቶች | ተቋም | ስልክ ቁጥር |
|---|---|---|
| • ጠቅላላ የመልሶ መክፈት ደንቦች<br>• የድርጅት የመያዝ አቅም ስሌት<br>• ደመወዝ መከላከያ መርሐ ግብር ብድሮች። ድህረ ገጽ ከዚህ።<br>• የኪራይ ማሻሻያና የማስወጣት ደንቦች። ድህረ ገጽ ከዚህ።<br>• የቤት ዉጭ ፍቃድ ማመልከቻ። | የኢኮኖሚ ልማት ቢሮ | (206) 684-8090 |
| • ያሉ የከተማ፣ ስቴትና ፌደራል ገንዘብ ድጋፍ ምንጮች።<br>• ለነጻ COVID-19 ምርመራ ምዝገባ። ድህረ ገጽ ከዚህ። | የደንበኛ አገልግሎት ቢሮ | (206) 684-2489 |
| • ጸረ-አድልዎ ማጋለ። ድህረ ገጽ ከዚህ። | የሲቪል መብቶች ቢሮ | (206) 233-7100 |
| • COVID-19 የማህበረሰብ ጤና ምከረ ሃሳቦች. ድህረ ገጽ ከዚህ። | ሲያትል-ኪንግ ካዉንቲ ማህበረሰብ ጤና | (206) 477-3977 |